# የአመፅ አዙሪት ተሰብሯል !!

ዮናስ

በሀገር ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና አመራሮቻቸው፣ በነፃ ፕሬስ ስም የተቋቋሙ ቅጥረኛ ጋዜጠኞችና የሙያ ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የኒዮ ሊበራሉ ኃይል ጉዳይ አስፈፃሚ የሆኑ የውጭ ሚዲያዎችና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት፤ በሰብዓዊ መብት ጥላ ሥር የተጠለሉ ምርጫ ታዛቢዎችና የሰብዓዊ መብት ተሟጓች ነን ባዮች ዘንድሮስ ምን እያሉን ይሆን?

እነዚህ ኃይላት ለአመፃ መነሻ ምክንያታችን ሲሉ የሚያቀርቡቱ ሁሉ ፍፁም ፀረ ዴሞክራሲያዊና ፀረ ልማታዊ አስተሳሰብ ሲሆን ሽፋናቸው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ልማትና መልካም አስተዳደር የመሳሰሉቱ ጉዳዮች ናቸው። ከውጭም ከውስጥም የሚገኙት እነዚህ ተዋናዮች ለሕዝቡና ለኢትዮጵያ በጎ ነገር እያሰቡና እየተመኙ እንደሆነ ቢያስመስሉም በተደጋጋሚ በመንግሥትም ሆነ በገዥ ሥርዓቱ እንደተገለፀውና በተግባርም እንደታየው ጉዳዩ ሕዝባዊነትና ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ግለኝነትና በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚደረግ  ሩጫ ነው። የውጪዎቹም ቢሆኑ ኢትዮጵያ በራሷ መንገድና ለራሷ የተመቹ አመራረጮችን ማየት መጀመሯ  ምኞታቸውን በማደናቀፉ ከላይ በተጠቀሱት ሽፋኖች ተመርተው ኢትዮጵያን የማተራመስ ፍላጎት ነው ይዘው የተነሱት።

በሀገራቸው ስላለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተንፍሰው የማያውቁት ተሟጋች ነን ባዮች፣ ከሀገራቸው አልፎ አህጉራችንን በመፈታተን ላይ ስላለው የአየር ብክለት ሹክ ብለው የማያውቁት ሚዲያዎችና ተሟጋች ነን ባዮች ደርሰው በተጠና መንገድ በሚከናወኑት እና ጠቃሚ በሆኑት ፕሮጀክቶቻችን ላይ ሁሉ በአየር ብክለትና በሰብዓዊ መብት ስም ጣታቸውን ይሰነቅራሉ። እነሱ ያሉትን እንደገደል ማሚቶ የሚያስተጋባው ፕሬስና የተቃዋሚው ጎራም ዙሩን ለማክረር ዳክሯል። ዳሩ ግን አዙሪቱ እስካሁን ከቀጠለ በኋላ ፍፃሜውን ሳያገኝ ከሰሞኑ የተሰበረበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

በተለይም የተቃዋሚው ጎራ ከሸሪኮቹ ጋር ሆኖ ተስፋ ባደረገው አማራጩ  በእርግጥም ለሥልጣን እንደሚያበቃውና ያለመውን ለመፈፀም እንደሚያስችለው እርግጠኛ ሆኖ ሰንብቷል፡፡ በምርጫ 97 ዋዜማ ላይ አባሎቻቸውና አጋሮቻቸው የነበሩት ከውስጥም ከውጭም የሚገኙ ሚዲያዎችን ጨምሮ ተሟጋች ነን ባዩን ሁሉ አሰባስበው ለዘመቻ ተሰልፈዋል፡፡ ዘማቾቹ የተሰጣቸው ተልዕኮ ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መታመም መሠረት በማድረግ የሞተዋል አዋጅ ማወጅና የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚል ጥያቄ እንዲያቀርቡ ነው።

ያ ካልሆነ ደግሞ ሀገሪቷ እንደምትበታተን በመለፈፍ ሕዝቡን ከሥጋት ላይ የመጣል ተልዕኮ ነበር ይዘው የተነሱት፡፡ ይህም ተብሎ…ተብሎ በነበር ቀረና የመላ ምት ፖለቲካ በሀገሪቱ አስተጋባ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰው ናቸውና፤ ከሁሉም በላይ ያለ እረፍት ሲሰሩ ስለኢትዮጵያ ኖረዋልና

ነውጠኛው ቀድሞ ቢያሚርትም ጊዜያቸው ደረሰና አቶ መለስ ማረፋቸው በእለቱ ለሕዝብ ተገለጸ፡፡ ትርምስና ብተና ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ አማራጪም እኛ ነን ሲሉ የከረሙት ነውጠኞች ከውጭ ያሉት የመግባት ዝግጅታቸውን ሲያጧጡፉ ከሀገር ውስጥ ያሉት ደግሞ የኮሽታ ድምጽ አድፍጠው ሲጠብቁ ሕዝቡ ሻማውን አብርቶ መሪውን በእንባ ተቀበለ፡፡ የአዙሪቱ ተዋናዮች ያከረሩት ገመድ ሊበጠስ ሰልጧል፡፡ የእነሱም ቆሽት እርር ድብን ብሏል፡፡

የሀዘን ሥርዓቱን በማጣጣልና ሀዘንተኛውን በመንቆር የአመጻ ዙሩን ወደነበረበት ለመመለስ ተሞከረ፣ ከሥርዓተ ቀብሩ በኋላ በኢህአዴግ ውስጥ የሥልጣን ሽኩቻ ተከስቷል የሚል የመለከት ድምጽ ከስብስቡ አካባቢ ተነፋ፡፡ ኢትዮጵያ አበቃላት ተብሎም ተጻፈ፣ ተነበበ፤ ፍፁም ግብረ ገብ በሆነ መንገድ ሙት ተወቀሰ ተዘለፈ፣ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር አይኖርም ተብሎም እገሌ እንዲህ አለ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እገሌ ነው፤ ህወኃት ሥልጣን አልለቅም ብሏል፡፡ ብአዴን ዘራፍ ብሏል፤ ኦህዴድ ለብቻዬን  እየዘፈነ ነው፤ ደኢህዴን ግራ ገባኝን እየዘመረ ነው፡፡ የሚሉና መሰል የከፋፋይና የሥጋት ዘመቻዎች ተጀመሩ፡፡ ሆኖም ግን ኢህአዴግ አቶ ኃይለማርያም ደሣለኝን እና አቶ ደመቀ መኮንንን የግንባሩ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀ መንበር አድርጎ በመምረጥ የሰለለውን የነውጠኛ ገመድ በጠሰው፤ የከረረውን አዙሪትም ሰበረው፡፡

የአመጹ አዙሪት በምን ምክንያት ተሰበረ? ገመዱስ እንዴት ተበጠሰ? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሳ ሦስት ነገሮችን በመመልከት ምላሹን ማግኘት ይቻለናል፡፡ የመጀመሪያው የአመጻው ባለቤቶች ራሳቸውን አለማወቃቸው ነው፡፡ የአመፃው ባለቤቶች የኢትዮጵያን ሕዝብና ኢህአዴግን አለማወቃቸው ደግሞ ሁለተኛውና ሦስተኛው ምክንያቶች ናቸው። ፈታ አድርገን እንየው፡፡

ለመድበለ ፓርቲ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በተጣለው ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረት ገዥውን ሥርዓት ለመቃወምና ራሱን ለሥልጣን የማብቃት የፖለቲካ ትግል የተጀመረው ከሽግግሩ ጊዜ ጀምሮ ነው። የሀገሬ ተቃዋሚዎች አሰላለፍ በውጭም ሆነ በውስጥ ይህ ነው የሚባል ትርጉም ያለው ሆኖ ካለመገኘቱም በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉና እየተጠናከሩ ይመጣሉ ሲባል ጉዟቸው ሁሉ የኋሊት እንደሆነ እስከ ዛሬ ዘልቋል። ተቃዋሚው ኃይል እርስ በርሱም አይተዋወቅም ስል ትግል የጀመረበትን ዘመንና አሁን ያለበትን ደረጃ በማጤን ነው።

እንደ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ዓላማው ሥልጣንና ለውጥ እስከሆነ ድረስ በፓርቲ ዲስፒሊን የመመራትና ገዥውን ሥርዓት ሊገዳደር የሚችል፤ አሳማኝ በሆነ መንገድ ተዘጋጅቶ በአባላቱ ክርክር ነጥሮ የወጣ ፕሮግራምና ስትራቴጂ እንደሚያስፈልግ የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም። ሆኖም ግን የሀገሬ ተቃዋሚዎችን ያየን እንደሆነ እርስ በርስም የተለየ አስተያየትና ሀሳብ ባላቸው ግለሰቦች የተዋቀሩና ለዲስፕሊን ተገዢ ባልሆኑ ልሂቃን የተሞላ ስብስብ ነው።

አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በእኔ አውቃለሁ ትምክህት የተወጠሩና ለውይይት ቦታ የሌላቸው በመሆኑ እርስ በርስ ያላቸውን ልዩነትና አለመግባባትም ወደ አባሎቻቸውና ሕዝቡ የሚያወርዱበት መንገድ ፍፁም ሥነ ምግባር በጎደለው ሁኔታና ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በዘለለ መንገድ ነው።

በምርጫ 97 ወቅት የተሰባሰቡትን እነዚህ ኃይሎች እንኳ ብናስታውስ ከላይ የተጠቀሱትን መገለጫዎቻቸውን ማረጋገጥ ይቻለናል። እርስ በርሳቸው ከመናቆር ጀምሮ ቦክስ የተማዘዙና የተወራረዱ፤ ካለ እኔ አይሆንም በሚል ትምክህት ሕዝብ የቸራቸውን ወንበር የረገጡ፣ ህግና ህገ ወጥነትን በማጣቀስ በፈጠሩት ትርምስም ወንጀለኛ ሆነው እሥር ቤት ገብተውም እንኳ ሲራገጡ የከረሙ ስለመሆናቸው ፀሀይ የሞቀው ሀቅ ነው፡፡ ከእሥር ተፈተው ከወጡም በኋላ ያሉበት ሁኔታ ያው የሚታወቅና በትርምስ የታጀበነው።

አንዳንዶቹ ፍፁም ሠላማዊ ትግልና ስለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ደንታ የሌላቸው በመሆኑና ህልማቸው ሁሉ በአቋራጭ ሥልጣን ላይ ፊጥ ማለት በመሆኑ አሸባሪ ድርጅቶች እስከ ማቋቋምም ደርሰዋል ።

ስለሆነም መጀመሪያ የውስጥ ሠላም ባጡ ስብስቦች የተቋቋሙ ፓርቲዎች፣ ለህግና የህግ የበላይነት ከመገዛት ይልቅ አመጽን አማራጭ ያደረጉ ኃይሎች፤ ሌላው ቀርቶ በአንድ ገበታ ላይ እንኳ ለመታደም የሚያስችል ተፈጥሮአዊና ፖለቲካዊ አመክንዮ በሌለበት ሁኔታ እንኳንስ ሕዝቡንና ገዥውን ሥርዓት ያውቋቸዋል ብሎ ለመገመት ይቅርና እርስ በርሳቸውም ቢሆን ስለመተዋወቃቸው ያጠራጥራል።

ስለሆነም ከምርጫ 97 ዋዜማ የጀመረውና እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ህልፈተ ህይወት የዘለቀው የትርምስና የአመጽ አዙሪት ራሱን በራሱ እያጨነገፈና እያኮላሸ ይህን የመሰለ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ሲደረግ ለመመልከትና ሳይወድ በግዱ እንዲቀበል አስገድዶታል፡፡

ተቃዋሚው ሕዝቡን አያውቀውም፤ አይተዋወቁም የምለው ደግሞ በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያውና ወሣኙ ነጥብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋና የተከበረ ስብዕና ያለው፤ ባላመነበት አካል ዝም ብሎ የማይነዳ ከመሆኑ የሚመነጭ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሕዝቡ እነዚህን ተቃዋሚዎች በየጋዜጣዊ መግለጫቸው ሮሮ ሲያቀርቡ እንጂ አማራጭ ፕሮግራማቸውን ይዘው ና ተከተለኝ ሲሉት አይቶና ሰምቶ አለማወቁ ነው፡፡

ከዚህም አለፍ ሲል አለውልህ ሲል የሚደሰኩረው ተቃዋሚ መሽቶ ሳይነጋ እርስ በርሱ ሲዘነጣጠል፣ ሲቧቀስ ያየውን ሕዝብ በሠላማዊ ትግል ሽፋን ለትርምስና አመጽ ማጨት ሕዝብን መናቅ እንደሆነ አልተገነዘበም፡፡ ስለሆነም በድህረ ምርጫ 97 አካባቢ የኢህአዴግ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት

ታክሎበት እና ባለማወቅ የተነሳ ለትርምስ ከተነሳው ኃይል ውጭ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህልፈተ ህይወትና የሥልጣን ሽግግር የቀረቡትን የትርምስ አመራጮች ሁሉ የሚሰማ ጆሮ ያለው ሕዝብ ቀርቶ ግለሰብም እንዳያገኙ አድርጓቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ገዥው ፓርቲ ለዘመናት የልማትና የመልካም አስተዳደር የእንጀራ ልጅ ሆኖ ለከረመው መላው ኢትዮጵያዊ በየቀየው የትምህርት፣ የጤና ተቋማት ግንባታዎችን ከነባለሙያው ማድረስ ችሏል፡፡ አዳዲስ የግብርና ልማት ቴክኖሎጂዎችን ከበቂ ባለሙያዎች ጋር አርሶ አደሩ ደጃፍ በማድረሱ፣ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን በማስፋፋቱ፣ አርሶ አደሩ ከማሳው ሳይነጠል የፍትህ አገልግሎት በማግኘቱ እና መሰል የልማትና የመልካም አስተዳደር ውጤቶች ባለቤት እንዲሆን በማስቻሉ ሕዝቡ እውቅናውን ለኢህአዴግ ስለመስጠቱና የአመጽ አዙሪቶች ሁሉ መሰበራቸውን በእንባው አረጋግጧል፡፡ ሌላውና የአመፃው ቡድን ሳይጀመር ላለቀው ሴራ ምክንያቱ ኢህአዴግን ጠንቅቆ ካለማወቅ የመጣ ነው፡፡

በመጀመሪያ ኢህአዴግ እና ኢህአዴጋውያን ወደ ጫካ ትግል ያመሩት በሕዝቦች ጫንቃ ላይ የተገደገደውን ቀንበር ለመሰባበር ነው፡፡ በዚህም ሂደት ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ባደረጋቸው በርካታ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ትግሎች በርካታ ልምዶችን በመቅሰም አሸንፎ ለመውጣት ቻለ፡፡ የከፈለበት ሥርዓትም ሕዝቡን ነፃ ለማውጣትና ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ከማስቻሉም በላይ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አብቅቶታል፡፡

በእነዚህና ከትጥቅ ትግሉ በኋላ ባሳለፍናቸው 21 ዓመታት ኢህአዴግ ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ከማድረግ አንስቶ የልማቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን
አድርጓል፡፡ በዚህ ሂደት የሚያጋጥሙ ስህተቶችን በመመካከርና በውይይት በመፍታት ሕዝብን በማዳመጥና ስህተቱን በማረም ሕዝባዊ ወገንተኝነቱን በማረጋገጡ ላለፉት 21 ዓመታት በውስጥና በውጭ በሚገኙ ጥገኛ የሀገሬ ሰዎችና የኒዎ ሊበራሉ ተላላኪ ኃይሎች የተጠነሰሱ ሴራዎች እዚያው ባሉበት ከስመዋል፡፡

ሌላውና የመጨረሻ አማራጭ አድርጎ የተመኘው የአመፃ መንገድ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈተ ህይወት ተከትሎ የሥልጣን ሽኩቻ ይኖራል ከሚል የተሳሳተ ግንዛቤ የመነጨ ስትራቴጂ ነው፡፡ ለዚህም ስትራቴጂ አንዱን በመሾምና ሌላውን በመሻር አራቱንም ብሄራዊ ድርጅቶችና አባላቱን ያናጫል ብለው ያሰቡትን ሁሉ በገደል ማሚቶዎቻቸው በኩል ሲያራግቡ ቢከርሙም እውነታው ሌላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩን የቀብር ሥነ ሥርዓት ከሕዝቡ የማይረሳ ሀዘን እና ድጋፍ ጋር በክብር ያከናወነው ኢህአዴግ በቀጣዩ ቀን ባደረገው የምክር ቤቱ ውይይት የግንባሩን ሊቀመንበር ባለመሰየሙ “ያልነው እውነት ሆኗል፣ እገሌና እገሌ መሣሪያ ተማዘዋል" እያሉ ያራገቡት የአመፃው

መሪዎችና ተዋናዮች በመንግሥት ቃል አቀባይ በኩል የተሰጣቸውን ምላሽ አስከ መስከረም 5 እና 6 ቀን 2005ቱ የኢህአዴግ ምክር ቤት ጉባዔ ድረስ መቀበል ተስኗቸው ነበር፡፡ ቃል አቀባዩ እንዳሉት "የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቦታ የመተካት ጉዳይ ቀላልና አንድን ጓድ ለበለጠ መስዋዕትነት ማዘጋጀት ነው" እንዳሉትም በመስከረም 5ቱ እና 6ቱ ጉባዔ ምርጫው ቀላልና ከኢህአዴግ ተፈጥሮአዊ ባህሪ የሚመነጭ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ያም ሆኖ ግን አቶ ኃይለ ማርያምና አቶ ደመቀን በመነጠል የባጥ የቆጡን ከማውራትና ከይችላሉ አይችሉም ንፋስ አመጣሽ ወሬዎች በመላቀቅ ስለኢህአዴግ የፓርቲ ዲሲፕሊን ለመገንዘብ መጣር ጠቃሚ የነበረ ይመስለኛል፡፡ ኢህአዴግ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ዲሲፕሊን የሚመራ ግንባር እንደ መሆኑ የፓርቲው አመራር በአቶ ኃይለማርያም ወይ በአቶ ደመቀ ወይም አባዱላ ብቻ የሚያዝ ሳይሆን በሕብረት የተያዘ ነው የሚሆነው፡፡ እንደ ኢህአዴግ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ዲሲፕሊን መሠረት ከላይ እስከ ታች የሚገኙት አመራሮች የሚመረጡት በቀጥታ በአባላቱ ወይም በተወካያቸው አማካይነት በድምፅ ብልጫ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የፓርቲው አባላት ከፓርቲው ዓላማ ሳይዛነፉ ጥያቄዎች ማንሳት፣ ችግሮች ላይ ውሣኔ የመስጠትና መፈትሄ የመሻት መብት አይኖራቸውም ማለት ሳይሆን ከበርካታ ክርክሮች በኋላ ለአብላጫ ድምፅ ተገዥ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የኢህአዴግ የፓርቲ ዲሲፕሊን በጋራ አመራር አሰጣጥ ላይ የጠበቀ መስመር ስለሚከተል በድርጅቱ ሊቀመንበርና በሥራ አስፈፃሚው መካከል ያለው የሥልጣን ርቀት ብዙ ትርጉም የሌለውና ለሥልጣን ሽኩቻ የሚያበቃ ቀዳዳ የሌለው ነው፡፡ ይህን ካለመገንዘብ ነው እንግዲህ ተቃዋሚው ኃይል ያቀዳቸው በርካታ ሴራዎች ሳይጀመሩ እዚያው የሚያልቁት። የፓርቲው ዲሲፕሊን እንደነሱ  በበልሃ ልበልሃ ሳይሆን ለአብላጫ ድምፅ የሚገዛ በመሆኑ ከታችኛው እርከን ጀምሮ የምትሰማ ኮሽታ  እዚያው ባለችበት ትሟሽሻለች፡፡

የሆነ ሆኖ ለተቃዋሞውና ለትርምስ ናፋቂዎች ሁሉ አንድ ነገር ብዬ ላጠቃልል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኢህአዴግ የተሻለ ፓርቲ እንደ ሌለ ሕዝቡ አረጋግጧል፡፡ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱን መሠረት በማድረግ ለተሰራው የመተካካት ፕሮግራምም ይሁንታውን ሰጥቷል። አመራሩም በተፈጥሮ አንዱ አንዱን መሆን እንደማይችል ተቀብሎ በጋራ አመራር እየሰራ መሆኑ ለዲሲፕሊኑ ያለውን ፅናኢነት የሚያሳይ ነው፡፡

ሕዝቡ ከሁሉም በላይ አጥብቆ ሠላም የመፈለግ ሁኔታውን በሚገባ አረጋግጧል፡፡ ይህ እምነት የተጣለበት መንግሥትና አስፈጻሚውም አጋጣሚውን በሚገባ እንደሚጠቀምበት እምነታችን የፀና ነው። አንዳንድ ጥገኞች ሽግግሩን የህወኃት ውድቀት ነው ቢሉትም እኔ ግን የህወኃት ድል ነው እላለሁ፡፡ ኢህአዴግ የሁሉም ኃይማኖት፣ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እንደሆነ ያረጋገጠበት ይህ ሽግግር፣ አስፈጻሚው እና ተተኪው ሰሞኑን የተፈጠረውን እና ያየነውን ኃያሉን የሕዝብ ማዕበል ከፊት አሰልፎ እቅዱን ለማሳካት እንደሚያስችለው አልጠራጠርም፡፡